


መስቀል ኃይላችን ነው ። መስቀል የነፍሳችን መድኃኒት ነው ።

# ትንሣኤ

እንኳን ከዘመነ ማርቆስ
ወደ ዘመነ ሉቃስ
አሸጋገረዎ





ዋጋው ሃምሳ ሣንቲም ቍጥር 14 ፲፱፻፸ ዓ.ም



www.ethiopianorthodox.org

‘‘ይህ መጽሔት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነትና ታሪክ ፡ ሥርዓትና ዜና ፡ ልማትና የግብረ ገብነት ትምህርት በተግባር ጭምር እንዲተረጐሙ ለሥራ እንነሣ የሚል ስለሆነ ‘‘ትንሣኤ’’ ተብሎ ተሰይሟል ።


አዘጋጅ
ሰይፈ ሥላሴ ዮሐንስ

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ
ሐዋርያዊ ድርጅት
የሥነ ጽሑፍ ክፍል ተዘጋጅቶ
በሁለት ወራት አንድ ጊዜ
እየታተመ የሚወጣ ።

የስልክ ቁጥር 116616
የመልእክት ሣ.ቁ. 3137
አዲስ አበባ


# ኦርእስት

ማውጫ — ገጽ


ደብዳቤዎች ........ ፩
አብ...ቱ ለቤተ ክርስቲያን ያስገኘው ለውጥ ........ ፪
ሁሉም ለውጥ ያስፈልገዋል ........ ፫
አሮጌውን ልብስ በአዲሱ ላይ የሚጥፍ ማነው ? ፤ ማንን እልካለሁ ? ........ ፬
ዘመን ካልሰሩበት አሮጌ ነው ........ ፭
የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ........ ፮
የጤና አምድ ፤ ትዳር እንደቀልድ አይመሰረትም ፤ ........ ፯
ፓትርያርኩ የነዘን መግለጫ መልእክት ላኩ ፤ ከ፴፫ ዓመታት በኋላ መጽሐፍ ቅዱስ በስሎቫክ ቋንቋ ታትሞ ወጣ ........ ፰
ዘመናዊ የንብ እርባታ እቅድ በእንደራቻ መድኃኒዓለም ቤ. ክርስቲያን . ፱
ካህናት መብትና ግዴታቸውን ይወቁ ........ ፲
የእግዚአብሔር ህላዌ ........ ፲፩
የመስቀሉ ነገር ........ ፲፪
ከቤተልሔም እስከ ደብረ ቁስቋም ........ ፲፫
አበቦችን ተመልከቱ ........ ፲፬
የመስቀሉ ቃል ........ ፲፭


# ደብዳቤዎች

ለትንሣኤ መጽሔት አዘጋጅ
ፖ.ሣ. ቍጥር 3137
አዲስ አበባ

ሰላምና ጤና ልዑል እግዚአብሔር ሰጥቶኝ ለመጀመሪያ ጊዜ ከእናንተ ውድ አባቶቼ ወንድሞቼና እህቶቼ ስተዋወቅ እና ሃይማኖቱ አሁን እንደምሰሶ ከሕይወቱ ጋር ተተክላ እንደማትነቀል ፈጣሪዬ ፊቱን ወደኔ ስላዞረልኝ ደስታዬ ቀንም ሆነ ማታ ወሰን የሌለው መሆኑን ስገልፅላችሁ ደስታ እየተሰማኝ ነው ።
አሁንም የማሳስባችሁ ጉዳይ ቢኖረኝ እናንተም ደብዳቤዬን እንብባችሁ እንደምትመልሱልኝ ደስታዬ ነው ። ጥዋት ተነስቼ ቤተ ክርስቲያን መሄድ ደስታዬ ነው ምንም ቀን አቋርጬ አላውቅም ሆኖም እንደሰዎች ዳዊት ለመድገም ሃሳቤ በጣም ይገፋፋኛል ሆኖም ትንሽ የገንዘብ እጥረት ስለያዘችኝ ምን ልሁን ሁልጊዜ በጣም አዝናለሁ ።

ስለዚህ ድርጅቱ እንደምንም ብሎ ለኔ ለዘላለም ሕይወቴን የምመራበት ጥዋት ጥዋት የምደግምበት ዳዊት በርዳታ መልክ እንድትለግሱኝ መልካም ምኞቴ ነው ይህም የማሳስባችሁ እደራ ጭምር ስለሆነ ተለመኑኝ ይህ ለኔ ትልቅ ርዳታ ነውና ለእናንተም እኔ በዚሁ ጉዳይ ከረዳችሁኝ እርግጥ ሁለተኛ የሕይወት መሪዬ እንደሆናችሁ ሁልጊዜ እንዳስብኋችሁ እኖርአለሁ ።

ከዚህ በተረፈ የልዑል እግዚአብሔር ሰላምና ጤና ከእኛ ጋር ሆኖ ከሰላሙና ከደስታው ጊዜ ያደርሰን ዘንድ መልካም ምኞቴ ነው ።

ውድ አሳሳቢያችሁ ተማሪ ፈቃዱ አበራ

● ተማሪ ፈቃዱ አበራ ሰው ዳዊት በመድገም ብቻ ይጸድቃል ማለት አይቻልም ። ሌሎችም የሚያስፈልጉ ብዙ ተግባሮች አሉና ነው ። ሥራ ራሱ ጸሎት ነው ። ራስህን ወይዳዊት ብቻ ሳታተኩር አባታችን ሆይ ብለህ እግዚአብሔርን ብትለምነው ቀና ልቡና ካለህ ይበቃሃል በሌላ በኩል ደግሞ ድርጅቱ ዳዊት እየገዛ የማያድል ስለሆነ ፍላጐትህን ለማሟላት ራስህ ብታስብበት መልካም ነው ።

✶✶✶

ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ
ሐዋርያዊ ድርጅት
አዲስ አበባ

የኦርቶዶክስ ሃይማኖትና የአብያተ ክርስቲያናትን መልእክትና ዜና ስከታተል ብቆይም አሁን ለመጀመሪያ ጊዜ በእግዚአብሔር ፈቃድ በደብዳቤ ስንገናኝ ምስጋና ይድረሰው እና ሃሳቤን ባጭሩ እገልጻለሁ ብዙ ጊዜ እንደ መጽሔት መጽሐፍ ፡ ጋዜጣ ፡ ወዘተ ስለ ቤተ ክርስቲያን ታወስልናላችሁ እስከ ናዝሬትም እየመጣችሁ ማዳረሳችሁ ግልጽ ነው እንደ አጋጣሚ እኔ ለሕክምና አ.አ. እንደመጣሁ ቂርቆስ ቤተ ክርስቲያን ተገኝቼ ቁ. 10 የምትል ትንሣኤ መጽሔት ደረሰችኝና ስመለከታት ጥሩ ትምህርት ሰጠችኝ አሁን ግን ልገልጽ የምፈቅደው ለሚመለከተው ክፍል 1 ስለ በዓላት አከባበር ፤ 2. መጽሔት ከማዘጋጀት ይልቅ በትንሽ ጥራዝ መጽሐፍ ቢሆን ? 3. ለመንፈሳዊው መልእክትና ለተጠቀሱት ዜማዎች በመጽሐፍ መልክ ብታቀርቡልን ? 4. ከ1 እስከ 30 የእግዚአብሔር አብ ስም በዓላቶች አሉ ይባላል እነ ማን ናቸው? በይበልጥ የሚከበሩትስ? 5. የእመቤታችን ቅ. ማርያም 33 በዓላት አሉ መቼና መቼ ይውላሉ? 6. ከእግዚአብሔር ጋር መገናኛ ጥሩ የጸሎት መጽሐፍ የባዓላት በጠቅላላው የዓመታት በአንድ ጥራዝ የተጻፈ እንዳለ ግለጹልኝ? 7. ስለ ሶቪዬት ባለፈው ጊዜ 146ኛውን ጳጳስ መረጠች ተብሏል ኢትዮጵያስ? ስንተኛውን ጳጳስ ነው አሁን የመረጠች? የመጀመሪያው ጳጳስ በስንት ዓ.ም. ተመረጡ? ማንስ ናቸው ? 8. ከአንዳንድ ሰው እንደምረዳው ከዚህ በፊት ጳጳሳት ከግብፅ እንደሚመጡ ሲገልጹልኝ ሁኔታውን አላብራሩልኝም ከግብፅ ከመቼ ጀምሮ እስከ መቼ መጡ? ስንትስ ጳጳሳት ናቸው? 9. ኢት/ በክርስትና እምነት ለብዙ ሺህ ዘመናት የቆየች የክርስቲያን ደሴት እየተባለች እንዴት የራሷ ጳጳስ አጥታ ቆየች? 10. 12ቱ ሐዋርያት ፣ 36ቱን ቅዱሳት አንስት 72ቱን አርድእት ብትገልጹልኝ? 11. 14ቱን ቅዳሴዎች የደረሱአቸው እነማን ናቸው? እዎን የማይገባ ሐሳብ ወይም ጥያቄ ቢኖር በመድኃኒታችን ስም ይቅርታ ይደረግልኝ መልሳችሁን በናፍቆት ነውና የምጠባበቀው በሚከተለው አድራሻ ጻፉልኝ

ቅዱስ ዮሴፍ ት/ቤት የመ ሣ.ቁ. 80
ትሬዛ በላይ ።
ናዝሬት

● እንደ ቤተ ክርስቲያናችን ሥነ ሥርዓት የሚከበሩት በዓላት 9 ሲሆኑ እነርሱም ፦

1ኛ/ መጋቢት 29 ቀን (ፅንሰት)
2ኛ/ ልደት
3ኛ/ ጥምቀት
4ኛ/ ቃና ዘገሊላ
5ኛ/ ደብረ ታቦር
6ኛ/ በዓለ ሆሣዕና
7ኛ/ በዓለ ትንሣኤ
8ኛ/ ዕርገት
9ኛ/ ጰራቅሊጦስ ናቸው

የሁለተኛው ጥያቄ መልስ መጽሔትና መጽሐፍ የተለየ አቋምና ቅርጽ ስላላቸው የእኛው መጽሔት ወርሐዊ ሲሆን መጽሐፍ ግን በአንድ ጊዜ ታትሞ የሚያበቃ ስለሆነ መጽሔት የሆነው በዚህ ምክንያት ነው ። 3ኛ ከአሁን ቀደም ያዘጋጀናቸው የመዝሙር መጻሕፍት አሉ ለወደፊትም ለማዘጋጀት ዕቅድ አለን ።

4. የእመቤታችን ቅድስት ማርያም በአላት መቼና መች እንደሚውሉ የተአምረ ማርያምን መቅድም ይመልከቱ ፤

5 ከእግዚአብሔር ጋር የሚያገናኝ ጸሎት መሆኑን ጠቅሰዋል መልካም አስተሳሰብ ነው፣ እኛም የምእመናንን አስተሳሰብ በማወቅ የጸሎት መጽሐፍ እሳትመናል መጽሐፉም በየሳምንቱ የሚጸለዩ የጸሎት መጽሐፍ ይላል ።

6/ ኢትዮጵያ ሦስተኛ ፓትርያርክ መርጣለች እርሳቸውም ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ናቸው ፡ የተመረጡትም ሰኔ 30 1968 ዓ.ም. ነው ።

7/ በኢትዮጵያ ውስጥ የተሾሙት ግብፃውያን ጳጳሳት በመጀመሪያ በአራተኛው መቶ ዓመት ከተሾሙት ከአቡነ ሰላማ ጀምሮ እስከ 1937 ዓ.ም. ከነበሩት እቡነ ቄርሎስ ድረስ 110 (አንድ መቶ አስር ) ናቸው ። የመጀመሪያው ኢትዮጵያዊ ጳጳስ ግን በኢትዮጵያውያን እንብሮተ ዕድ የተሾሙት በ12ኛው ምዕት ዓመት የነበሩት ጻድቁ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ናቸው ።
ከዚያም በፊት ሆነ ከዚያ በኋላ ኢትዮጵያውያን የራሳቸውን ጳጳሳት ሳይሾሙ የቀሩት የጵጵስናው ማዕርግ ለጊዜው በእስክንድርያ በነበረው መንበረ ማርቆስ ተይዞ በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ላይ ተፅእኖ ስለነበረ ነው ።

8/ ስለሐዋርያት ስም ዝርዝር ማቴ.ም. 10 ይመልከቱ ።

9/ 14ቱን ቅዳሴ ስለጻፉት ሰዎች ለማወቅ መጽሐፈ ቅዳሴን ይመልከቱ ።

ከዚህ በተረፈ ጥያቄውን በሙሉ በዝርዝር ለመግለጽ ደስ ባለን ነበር ግን ያለን የመልስ መስጫ አምዳችን አጭር በመሆኑ ነው ስለጥያቄዎ እናመሰግናለን ።



www.ethiopianorthodox.org

# አብዮቱ ለቤተ ክርስቲያን ያስገኘው ለውጥ

ርእሰ አንቀጽ

አቢድ የተባለ ምሁር የዓለምን ተፈጥሮ ሲመረምር ቀዋሚ ነገር ለውጥ መሆኑን ስለደረሰበት "ሁሉም አላፊ ነው
ተዋሚ ነገር የለም አንድ ተዋሚና ኗሪ ነገር ቢኖር እርሱ ለውጥ ብቻ ነው ሁሉም ይመጣል፣ይሔዳል፣ይገለባበጣል
ያልዋወጣል የሚወለደውም ሁሉ የለውጥን ፍሬ በማጎጸኑ እየጸነሰ ይወለዳል" ሲል ተናግሯል በዚሁ አንፃር አብዮ
ቱ ለቤተ ክርስቲያን ያስገኘውን ለውጥ ስንመለከት የዛሬይቱን ቤተ ክርስቲያን ወደጥንታዊቷ ቤተ ክርስቲያን እን
ደመለሳት እንረዳለን ። ምክንያቱም በሐዋርያት ዘመን የነበሩት ክርስቲያኖች ገንዘባቸውን በሐዋርያት እግር አጠ
ገብ አስተምጠው እንደየቤተሰባቸው ብዛትና ለሚያስፈልገው መንፈሳዊም ሆነ ሥጋዊ አገልግሎት ይካፈሉ ስለነበ
ር በየአንዳንዳቸው ላይ ችግር እንደሌለባቸው መጽሐፍ ቅዱስ ይነግራልና ነው ።

በመሠረቱ ኢትዮጵያ ከጥንት ጀምሮ ሥልጣኔዋንና የትምህርት ልግቷን መሥርታ የቆየችው በቤተ ክርስ
ቲያን አካባቢ መሆኑን ማንም አይዘነጋውም ። የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የሃይማኖት ቦታ ብቻ ነች ብሎ ማመን
ፍጹም የተሳሳተ ነገር ነው ። ማንኛውም ሰው ትምህርትን ለመማርና ዕውቀትን ለማስፋፋት በፈለገ ጊዜ ርዳታ ያ
ገኝ የነበረው ከቤተ ክርስቲያን መሆኑ ይታወቃል ። ታዲያ ይህ ሁሉ ውለታዋና ታሪኳ እንዲረሳ ያደረገው ያለፈው
መንግሥት አስተዳደር ነው ።

ሌላው ተርቶ የደብር አለቆች ሲሾሙ የነበሩት በንጉሡና በመኳንንቱ በመሆኑ አስተሳሰባቸው ሁሉ በማን
አሉብኝ የተመሠረተ ስለሆነ የሾሟቸውን ጌቶቻቸውን እንጂ ቤተ ክርስቲያንን አለማገልገላቸውን ከሥራቸው ልን
ረዳ እንችላለን ። የቤተ ክርስቲያን አስተዳደር ተዛብቶ የተገኘው የቤተ ክህነት ሹማምንት በካህናትና በምእመናን
ምርጫ ባለመሾማቸው መሆኑ ግልጽ ነው ።

ከየካቲት ፷፮ ዓመተ ምሕረት ወዲህ ግን አብዮቱ ለቤተ ክርስቲያን ያስገኘው ለውጥ ትክክለኛውን የጥን
ቱን አመራር ይዛ እንድትጓዝ አድርጓታል ብንል ከእውነት የራቀ አይደለም ምክንያቱም በገጠር መሬቱን ፣
በከተማ የቤት ኪራዩን የቤተ ክርስቲያን ትምህርት የሌላቸው ሰዎች በቤተ ክርስቲያን አመካኝተው ትክለኛ
ነን በማለት ሲበዘብዙ የነበሩትን አብዮቱ አስወግዶአቸዋልና ነው ።

ታዲያ ቤተ ክርስቲያን መብትና ግዴታዋን አውቃ በለውጡ አንፃር ትራመዳለችን? አገልጋዮቿንስ አው
ታለችን? ራሷን በራሷ የማስተዳደር መብት የተሰጣት ስለሆነች የአመራሯን ሒደት ከምእመናን ጋር አስተባብራ
ወደፊት ካልተራመደች የአስተዳደር ተሐድሶ ታገኛለች ለማለት አያስችልም ። ጥፋቱም የቤተ ክርስቲያን መሪ
ዎችና አገልጋዮች እንጂ የምእመናን እንደማይሆን ግልጽ ነው ። ምክንያቱም የቤቱን ችግር የሚያውቀው የቤተ
ሰቡ ኃላፊ እንደመሆኑ የቤተ እግዚአብሔርንም ችግር ከእነርሱ የበለጠ ሌላው ሊያውቀው አይችልምና ።

ይልቁንም ግንባር ቀደም በመሆን ሲያገለግሉ የነበሩት ካህናት ዛሬ በሰበካ ጉባኤ ፣ በአድባራትና ገዳማት
ካህናት ሰብከተ ወንጌል ማኅበር እየተደራጁ በትክለኞች ቶፋ እየተባሉ ይጠሩበት የነበረውን ስም ወደጋን እንዲ
ለውጡት ያስፈልጋል ።

በሌላ በኩል ደግሞ "ሰው ከአካባቢው ይማራል" እንደሚባለው ሁሉ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን አገልጋ
ዮች ካህናትም ከኢትዮጵያ አብዮት ብዙ ሊማሩ ይችላሉ ። ለውጡ በነማን ተጀመረ? እነማን ከሥልጣናቸው ወረዱ
ትርጉሜቸ ወይስ ግንዱ? ብለን ስንመረምር የአብዮቱ የሂደት ታሪክ ያስረዳናል ይህ ከሆነ " እንደ ርግብ የዋህ እን
ደ እባብ ብልህ ሁኑ" ብለው የሚያስተምሩት ካህናት አብዮቱ ያስገኘላቸውን የራስ መቻል መብት ግዴታቸውን
እያሟሉ ካልተጠተሙበት ምንጊዜም ሠፈራቸው የእውነተኞች ካህናት ቦታ ስለማይሆን ዛሬውኑ በመብታቸው
ይጠቀሙበት እንላለን ።



# ሁሉም ለውጥ ያስፈልገዋል ።

ከአለቃ ነቢየልዑል ዮሐንስ

አንዳንድ ሊቃውንት ሲናገሩ ለውጥ ያስፈል
ጋል ቢባልም ለውጡ ሥነ ሥርዓትን የተከተ
ለ መሆን አለበት ሥነ ሥርዓት ያልተከተለ ለ
ውጥ የኑሮ እንቅፋት ሲሆን ሥነ ሥርዓት የተከ
ተለ ለውጥ ግን የሕይወት ዝግጅት ነው ይላሉ ።

ሌሎቹ ደግሞ ለውጥ እውነተኛ ከሆነ ለፍሬ
ያማ ውጤት ሕዝብን ሊያዘጋጅ ከመቻሉም ሌላ
ለውጥም እራሱ የመልካም ኑሮ ጉዞ ነው የሚል
አስተያየት ይሰጣሉ እርግጥም ካሁን ቀደም በዓ
ለም ታይቶ የማይታወቅና የዓለምን ሕዝብ ያስደ
ደነቀው የካቲት 66 ዓ.ም. በኢትዮጵያ የተደረ
ገው የብዙሃኑ ሕዝብ የለውጥ እንቅስቃሴ ነው
ለሁሉም ለውጥ ያስፈልገዋል የተባለውም ስለ
ዚህ ነው ።

ይህን የማይከተል ለውጥ ግን የስም እንጂ
የተግባር ስላይደል ውኆንብርን ከመፍጠር
በቀር ጥቅምን አይሰጥም ለምሳሌ አንዱን ጠር
ሙስ ውሃ ወደ ባዶ ጠርሙስ ቢገለብጡት ከማ
ፋሰስ በቀር ለውጥ አይሆንም ።

በተጨማሪም በትልቅ ድስት የሚሠራውን
ወጥ በትንሽ ድስት ቢሠሩት ወጡን ስለማያጣ
ፍጠው ተለወጠ ሊባል አይቻልም በሌላ በኩል
ደግሞ ቀኑ በሳምንት ፡ ሳምንቱ ፡ በወር ፡ ወሩ ፡
በዓመት እየተቀያየረ ዘመኑ ተለውጦ አዲስ
ዘመን ሆነ ቢሉት ዘመኑ በሥራ ፡ ለሥራ ካልተ
ለወጠ አሠሪዎችና ሠራተኞችም በሥራ ተለዋ
ውጠው ካልታደሱ ለሁሉም ለውጥ ያስፈልገ
ዋል የተባለው አነጋገር ትርጉም አልባ ሆኖ
ይቀራል ።

ይህን ሁሉ ያተትንበት ዋናው ምክንያት
የቤተ ክርስቲያናችን አስተዳደር በሁሉም ነገር
ለውጥ ያስፈልገዋል ለውጡም ሥነ ሥርዓት የ
ተከተለ መሆን አለበት ለማለት ነው ለምሳሌ
ቤተ ክርስቲያናችን በየዓመቱ ዘመን ተለወጠ
አሮጌው ዘመን አልፎ አዲሱ ዘመን ተተካ በማ
ለት ስታስተምር ኖራለች ብዙ ዘመናትንም
ለዋውጣለች የራሷን አስተዳደር ሠራተኞችዋ
ንና ፡ ሥራዋን ግን እስከ አሁን አለወጠችም ።

በዚህ አኳኋን ለውጥ የማይከተል የቤተ ክር
ስቲያን አስተዳደር ሥነ ሥርዓት ስለሌለው ከሃ
ሳባችን ከሥራችንና ፣ ከሕይወታችን ጋር ስለማ
ይራመድ ፣ በቤተ ክርስቲያን በኩል ለውጥ አለ
ለማለት አያስደፍርም በዚህ መንገድ ከተጓዝ
ን ወደ ተፈለገው አቅጣጫ ለመመራትና ጥቅ
ምን ለማግኘት አይቻልም ይህም ማለት የመሸ
ጋገሪያ ዘመንና ለውጥን በአንድ እጅ ጥቅምን
በሁለተኛ እጅ ይዞ መራመድ አዋቂነትንና ልም
ምድን ከመጠየቁም በላይ ቁርጥ ውሳኔ ኅብረት
ን አጣምሮ መያዝ ስለሚያስፈልግ ወደ ክፉ
ፈተና እንዳንገባ መጠንቀቅ አለብን ።

ይሁን እንጂ ለውጥ እንግዳ ነገር አይደለም
የመጀመሪያዪቱም ቤተ ክርስቲያን የተገኘችው
በለውጥ ነበር ። በዚህም መሠረት ክርስቶስ አሪ
ትንና በኦሪት ስም የነበረውን መጥፎ ልማድ ሲ
ለውጥ በኦሪት ሊተካ የሚገባውን ወንጌል ሰበ
ከ አዲስም ሕግ አወጣ ፣ አዲስ ሥነ ሥርዓትም
ለሕዝቡ አስተማረ እኛም የክርስቶስ ተከታ
ዮች ከሆን ጉልቻ ቢለዋወጥ ወጥ አያጣፍጥም
እንደተባለው ሁሉ በቤተ ክርስቲያናችን እገሌ
ይነሣ እገሌ ይውረድ ከማለታችን በፊት በመጀ
መሪያ ቤተ ክርስቲያን ሰዎችዋን ትወቅ ፣ ሰዎች
ም ቤተ ክርስቲያንን ይወቅዋት ቀጥሎም ለሰ
ዎችዋ ንቃተ ሕሊና ትስጥ ይህ ከሆነ ለሁሉ
ለውጥ ያስፈልገዋል የተባለው አነጋገር በሥራ
ላይ ሊውል ይችላል ።

"አመርስን የተባለው ፈላስፋ ስለ ለውጥ ሲ
ናገር መልአክ ወደ ሰው ቢለወጥ ለውጡ አስተ
ማማኝ አይደለም ሰውግን ወደመልአክነት ቢለ
ወጥ በተግባር ስለሆነ ለውጡ አስተማማኝ
ነው" ብሏል እንዳለውም የቤተ ክርስቲያን አስ
ተዳደር ከሰዎቹና ከሥራው ጋር መለወጥ ይፈለ
ለግበታል ።

ይሁን እንጂ አንዳንድ ለጥቅም የተገዙ ሰዎች
ለውጥን አይፈልጉም ስለዚህ ከለውጥ እራሳቸ
ውን ለመደበቅ ያስባሉ ፣ ለውጡም እንደ እሥ
ር ቤት መስሎ ይታያቸዋል የተለመደውንና ም
ቹውን ቦታ የሚያስለቅቃቸው እየመሰላቸው
ለውጡን በጣም ይፈሩታል አንዳንዶቹም ከለ
ውጡ እራሳቸውን በማግለልና ባለመግባባት
ራሳቸውን ሲበድሉ ይገኛሉ እንዲህ ያለው ተግ
ባር የለውጥ ተቃራኒ ነው ።

ለምሳሌ ለውጥ አስፈላጊ በመሆኑ ክርስቶስ ሐ
ዋርያትን በሥራቸው ሕዝብን እንዲለውጡ
ወደ ዓለም ልኳቸዋል በለመዳችሁት አካባቢ
ና ብዙ ችግር በሌለበት ቦታ አስተምሩ አላላቸ
ውም እነሱም በታዘዙት መሠረት ዓለምን በሥ
ራቸው ለውጠውታል ለቤተ ክርስቲያንም አዲ
ስ ለውጥ አምጥተዋል ፣ ቤተ ክርስቲያናችንም
በዚህ ዓላማ እየተመራች አዲስ ለውጥ ለማ
ሳየት ይገባታል ከላይ እንደ ተነገረው ዓለም
ን በእግዚአብሔር ቃል የለወጥዋት አሥራ
ሁለት ደቀ መዛሙርት እንጂ ብዙ ሰዎች
ስላይደሉ ቤተ ክርስቲያናችንም ሰዎችን በ
ትምህርት ለመለወጥ ከፈለገች በብዛት ላይ
ሆን በጥራት አምና ሰዎችዋን መምረጥ አለባት
ምርጫውም በዚህ መንገድ ከተመራ ጠቅላላ
ው አግኝ ጥቅሙንና ጉዳቱን ለይቶ ስለሚያ
ውቀው የሚያደረገው ለውጥ የአንድነት ፡ የኅብ
ረት ሊሆን ይችላል ነገር ግን ጨለማን ተገን
አድርጐ የሰውን ስም በማጥፋትና የእያንዳንዱ
ን የሰው ስም ተግባር የሚያረክስ ወሬ በማዛ
መት በቤተ ክርስቲያን ላይ ታላቅ ውድቀትን
ከማምጣቱም ሌላ በምዕመናን መካከል መለያ
የትን ይፈጥራል ስለዚህ የምንሠራው ሥራ
ሁሉ መልካም ለውጥ እንዲያመጣ በብርሃንና ፡
በአደባባይ ይሁን ብርሃናችሁ በሰው ፊት ይብ
ራ ተብሏልና ።

ለምሳሌ ከዚህ በፊት የነበረው የወደቀው
የዘውድ መንግሥት ወደ ኅብረተሰብአዊነት
እንደተለወጠ ሁሉ ቤተ ክርስቲያንም ይህን የ
መሰለ ለውጥ ቢያደረግላት ለውጡ ሥርዓት ሊኖ
ረው ይችላል ። ይህ ካልሆነ በቤተ ክህነት አስ
ተዳደር በኩል እገሌ ይነሳ እገሌ ይውረድ የሚለ
ው አነጋገር ቤተ ክርስቲያንን ሊለውጣት አይች
ልም ሰላምንና ፍቅርን ከማሳጣቱ በቀር ለካህ
ናቱ ሆነ ለምዕመናኑ የመንፈስ ለውጥ አያመጣ
ላቸውም የቤተ ክርስቲያንንም መታደስ የአስ
ተዳደርንም መሻሻል አያስገኝም ።

እንግዲህ አሠሪዎችም ፡ ሠራተኞችም የሆን
ሁሉ ለውጥ ወዳጆች ከሆን የቤተ ክርስቲያንን
አስተዳደር ለውጥ ከመጠበቃችን በፊት መጀ
መሪያ ራሳችንን መለወጥና ማደስ ያስፈልገና
ል ፡ እርጊ ሰውነታችንን ከነሥራው ገፈን ጥለን
ለለውጥ እንዘጋጅ እኛ ካልተለወጥን ሌላውን
ለመለወጥ እንችልምና ።



www.ethiopianorthodox.org

# አሮጌውን ልብስ በአዲሱ ላይ የሚለጥፍ ማነው ?

ከቄስ ልሳነ ወርቅ በዛብህ

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ይህንን ኃይለ ቃል ለደቀ መዛሙርቱ ሲያስተምር ዘመኑ የለውጥ ዘመን ነበር ፤ ያን ጊዜ ሕዝቡን ከአሪት አስተዳደርና ልማድ ፈጽሞ አላቆ ወደ ሕገ ወንጌል ጕዳና ለመመለስ ከፍ ያለ መሥዋዕትነትን ጠይቋል ያንንም መሥዋዕትነት ለመቀበል በመጀመሪያ የተዘጋጁት ሐዋርያት ነበሩ ።

ሐዋርያት አዲሱን ሕገ ወንጌል ለዓለም ሕዝብ ለማዳረስ ተዘጋጅተው ሲነሡ ሌላ ምድራዊ ኃይል አልነበራቸውም ከአሮጌነት የሚያድስ ፤ የሚያጽናና መንፈስ ቅዱስም ገና አልተላከላቸውም ነበር ፤ በመንፈስ ቅዱስ ኃይልም ስ ውነታቸው ስላልታደሰ እሳቱንና ስለቱን ችግሩንና መከራውን ደፍሮ ለመቀበል እጅግ በጣም የሚያዳግታቸው መሆኑን ራሱ ክርስቶስ ተመልክቶ ሁለት ምሳሌዎችን አስተምሯል ።

"ከአረጀ ልብስ ላይ አዲስ እራፊን የሚጥፍ ማነው? መጣፊያው ልብሱን ይቦጭቀዋልና ፤ መቀደዱም የባሰ ይሆናል በአረጀም እንሥራ (አቅማዳ) ያልፈላ (ጉሽ) ጠጅን የሚያኖር የለም ። ቢያደርጉት ግን እንሥራው ይሠበራል ጠጁም ይፈሳል " ይልና "ነገር ግን አዲሱን (ያልፈላውን) ጠጅ በአዲስ እንሥራ ያደረጉት እንደሆን እርስ በእርሳቸው ይጠባበቃሉ" ይላል (ማቴ.9.16-17 )

ይህ ትምህርት በአሁኑ ጊዜ በቤተ ክርስቲያን አንጻር ሊታይ የሚገባው ነው ቤተ ክርስቲያናችን አሁን የምትገኘው በአሮጌና በአዲስ ዘመን መሸጋገሪያ ላይ ነው ፤ የቆየውን አሮጌ ሥርዓት ትታ አዲሱን ሥርዓት ለመተካት ከፍ ያለ ተጋድሎ ይጠብቃታል ፤ የቤተ ክርስቲያን ባለስልጣኖችም መንፈሳቸው ያልታደሰ ስለሆነ በሚሠሩት ሥራ አይተማመኑም አንድአንዶቹ ደግሞ ችሎታ እያላቸው ፈሊጥ የጐደላቸው ይሆኑና ለሥራው እንቅፋት ይሆናሉ፤እንዲሁም ሌሎች ጊዜው ያለፈበትን አሮጌውን አሠራር ከአዲሱ ጋር አጣምረን እንሠራለን በማለት ቤተ ክርስቲያንን ባለችበት እንድትረግጥ ያደርጓታል ። ይህም ከችሎታ ማነስ የሚፈጸም ድርጊት ብቻ ሳይሆን ከፈሊጥም ጉድለት ጭምር በመሆኑ የቤተ ክርስቲያን ባለሥልጣኖች ሁሉ ችሎታንና ሃይማኖትን ከፈሊጥ ጋር ገንዘብ ማድረግ አለባቸው ስለዚህ አንድ ተመራማሪ ሊቅ ሲናገር የዚህን ዓለም አዲስ እርምጃ የሚያደናቅፉት ሦስት ነገሮች አሉ ይልና በዝርዝር ሲያስረዳ ፈሊጥ የሌለው ሃይማኖት መሥራት የሌለበት ችሎታ የማይሰጡበት ገንዘብ ናቸው" ይላል ።

በአሁኑ ጊዜ ፈሊጥ ከሃይማኖት ጋር ችሎታ ከመሥራት ጋር አጣምሮ ይዞ ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችንን በሚገባ ማገልገል እጅግ ተፈላጊ ነው ፤ ወደፊት ቤተ ክርስቲያናችን ባህሏንና ሥነ ሥርዓቷን አክብራ ለመኖር የምትችለው እንደርግብ የዋህ እንደ ዕባብ ብልህ የሆኑ ሊቃውንት ሲኖሩዋት ነው ።

ቀደም ያለ ታሪክን ስንመለከት በቤተ ክርስቲያናችን አካባቢ ለካህናትም ሆነ ለምዕመናን ተስማሚ ያልሆነ የተመሰቃቀለ አሠራርን እናገኛለን ለምሳሌ ቤተ ክርስቲያንን እንዲያስተዳድሩ አለቅነት የሚሾሙ ከቤተ ክርስቲያን ጋር የትምህርት ግንኙነት የሌላቸው በዕውቀታቸው ዝቅተኞች የሆኑ የስም ካህናት ነበሩ ። እንዲሁም በዓመት በዓል ለግብር የሚኮለኮሉትና ስለቤተ ክርስቲያን ጉዳይ የሚጠየቁት ሊቃውንቱ ሳይሆኑ ከቤተ ክርስቲያን ትምህርት የተራቆቱ ናቸው ከምሁራኑ ይልቅ የቤተ ክርስቲያንን ሀብት የሚበዘብዙት ትክክለኛውን ሥራቸውን ትተው ለባለ ሥልጣኖች ጕንበስ ቀና የሚሉ ተከበስባሾችና ተቅለሽላሾች ውዳሴ ከንቱን ቀማሚዎች እንደነበሩ ሁሉም የሚያውቀው ነው ።

አሁንም ቢሆን ቤተ ክርስቲያናችን እንደዚህ ካለው መጥፎ ተግባር ፈጽማ የተላቀቀች አይመስልም የምታደርገው ለውጥ ሊሠምር የሚችለው በውጭ ሀገርም ሆነ በሀገራቸው ትምህርት የበለጸጉ ሊቃውንት ሙሉ በሙሉ የሥራው ተሳታፊዎች ሆነው ሲገኙ ነው ነገር ግን እስከ አሁን ድረስ ቤተ ክርስቲያን ወደ ውጭ ሀገር የምትልካቸው ሊቃውንት በርከት ያሉ ሲሆኑ ተቀብላ በሥራ ላይ የምትመድባቸው ግን በጣት የሚቆጠሩ ናቸው ።

ስለዚህ ቤተ ክርስቲያን በሊቃውንቷ ብትጠቀም መልካም ይመስለኛል ።

# ማንን እልካለሁ ?

ከበለጠ አበበ

በፊታችን ብዙ ዓይነት ሥራዎች ተደቅነው የሠራተኛ ያለህ እያሉ ይጮሃሉ ፤ በአሠሪነት የተመደቡ ክፍሎችም ሥራውን ለማሠራት ትጉህና ራስ ወዳድ ያልሆኑ ሠራተኞችን ለመምረጥ ይጥራሉ ፤ በተለይም በአሁኑ ዘመን በለውጥ እንግር የታደሱ ሠራተኞች ይፈለጋሉ ከሌሎችም በፊት ለሥራ ተመርጠው ይላካሉ ቢሆኑም ለተፈለገው ሥራ በብቁነት የሚመረጡና የሚላኩ አልተገኙም ። ስለዚህ ነው እግዚአብሔር "ማንን እልካለሁ? ሲል ያለውን ችግር የገለጸው ።

እግዚአብሔር አስቀድሞ ኅብረተሰቡን በመንፈሳዊ አመራር (ገንብቶ) አደራጅቶ የሚያገለግል እንደገናም እምላክነቱን ለሕዝብ የሚያስረዳና ሕዝቡን ከእግዚአብሔር የሚያገናኝ ታማኝ አገልጋይ ይፈልግ ነበር ፤ እግዚአብሔር ይህ ዓይነቱ አገልግሎት ብቻ ብቱ ነው አላለም ፤ ሠርቶ የሚያሠራ እምነ የሚያሳምን ፤ ስለሰላምና ስለፍቅር ስለእኩልነት የሚያስተምር የሰላም መልእክተኛ ይፈልግ ስለ ነበር "ማንን እልካለሁ?" አለ ዳሩ ግን ሊላክ የሚቀርበው ተመራጭ ከራስ ወዳድነት የተነጣ የራሱ ኑሮ የሚ

ወደ ፤ኛው ገጽ ፡ የዞረ



# ዘመን ካልሰሩበት አሮጌ ነው

ሰዎች በዚህ ዓለም ላይ ሲኖሩ እድሜአቸው እንዲረዝም የሚመኙ ጥቂቶች አይደሉም ።

በዚህ ዓለም ላይ ረዥም ዘመን የመኖር ጥቅሙም ያ ሰው ብዙ እንዲያውቅ በእውቀቱም አገሩንና ወገኑን እንዲጠቅም ጥሩ ሥራ ሠርቶ ለራሱና ለቤተሰቡ እንዲረዳና የእግዚአብሔርንም ሕግ እንዲፈጽም እንጂ በከንቱ አይደለም ። ብዙዎችም በረዥሙ ዘመናቸው ሳይጠቀሙበትና ምንም ሳይሰሩበት በከንቱ ያሳለፉ እንዳሉና አንዳንዶቹም ዘመናቸውን የተጠቀሙበትና ብዙ የሠሩ እንዳሉ መጽሐፍ ቅዱስ አጣርቶ ያስረዳናል ።

ለምሳሌ ያህል የማቱሳላን የሕይወት ታሪክ ስንመለከት ማቱሳላ ፱፻፷፱ ዓመት እንደኖረና ብዙ ሴቶችና ወንዶች ልጆች እንደወለደ ይናገራል እንጂ ማቱሳላ ለኅብረተሰቡ ይህንን ሠራ ይህንን አቋቋመ ወይም አስተማረ የሚል አናገኝም ሌሎችም እንደዚሁ ብዙ ዘመን በዓለም ላይ ኖረው ምንም ሳይሠሩ ያለፉ ጥቂቶች አይደሉም ። እንግዲህ የነዚህ ሰዎች በዓለም ላይ መኖር ምን ጥቅም ይሰጣል ? ለነዚህ ሰዎችስ ዘመን ቢለዋወጥ ማርቆስ ሄዶ ሉቃስ መጣ እያሉ ከመቁጠርና የሄደው አሮጌ ዘመን ተመልሶ ከመምጣቱ በስተቀር ምን ትርጉም ይሰጣቸዋል ? ምንም ትርጉምና ጣእም አይሰጣቸውም ።

ነገር ግን የአብርሃምን የሕይወት ታሪክ የተመለከትን እንደሆን አብርሃም ፻፸፭ ዓመት ሲኖር ለሃገርም ለእግዚአብሔርም ብዙ ሥራ ሠርቷል ሌሎችም እንደዚሁ በዘመናቸው ብዙ የሠሩ እንዳሉ ታላቁ መጽሐፍ ይናገራል ።

እዎን ያለፉት በዘመናቸው የሠሩም ያልሰሩም እንዳሉ ሁሉን ከታሪክ እንማራለን ። እኛስ ባለፉት ዘመናት ምን ሠራን? ብለን ለጥቂት ደቂቃ እስቲ ራሳችንን እንመርምር ገበሬው የግብርና ሥራውን ብርዱንና ሐሩሩን ሳይፈራ በደንብ ሰርቷል? ነጋዴው በእውነት ሳይዋሽ ሳይቀጥፍ ነግዷል? የቢሮ ሠራተኛው ቢሮክራሲን ሳያበዛ በእውነት የሚፈለግበትን ለአገሪቱ የሚጠቅመውን ሥራ በደንብ ሠርቷል ? ካህኑ ለእግዚአብሔር መንግሥት መስፋፋት በእውነት ቃለ እግዚአብሔርን አዳርሷል ? አስተማሪው እውቀትን ለተማሪዎቹ አበርክቷል? ተማሪውስ ያለ ግብዝነት በእውነት እውነተኛውን እውቀት ቀስሟል ? ወዛደሩ የአገሪቱ ምርት ከፍ እንዲል ያለ ምንም ልግመት ሠርቷል? በጠቅላላው ኅብረተሰቡ በተሰማራበት ሥራ ለአገር እድገት ለወገን ጥቅም ለራስ ሰላም የሚሆነውን በእውነት ስለእውነት በዘመኑ ሠርቷል ?

በእውነት ሁሉም የሚፈለግበትን የሥራ ድርሻ በዘመኑ ሠርቶ እንደሆነ ምንም አይዐዐትም ። ዘመኑም ለርሱ አዲስ ዘመን እንጂ አሮጌ ዘመን አይሆንበትም ይኸውም አዲስ የሥራ እቅድ ስላለው ነው ። ካልሠራበት በዋዛ ፈዛዛ በወሬ ብቻ አሳልፎት ከሆነ ግን አሁን የያዘው አዲሱ ዘመን አዲስ መሆኑ ቀርቶ አሮጌ ዘመን ይሆንበታል ። ምክንያቱም አዲሱንም ዘመን የሚጠብቀው አሮጌ ጠባዩ ወይም ያው ዋዛ ፈዛዛ ስለሆነ ነው ። ዘመን መያዣ መጨበጫ የሌለው ስለሆነ ካለፈ በኋላ ከወይኔ በቀር ምንም ሊባል አይቻልም ። ሥራ መሥራት በጊዜ እንጂ ጊዜ ካለፈ መሥራት አይቻልም ተራው የሌላ ነውና ።

ከላይ እንደገለፅነው ብዙ የታሪክ ሰዎች ሁነው የሚነገርላቸው ሁሉ በዘመናቸው ደከመኝ ሰለቸኝ በረደኝ ሳይሉ ደመና ሆነ ዝናም ሳያግዳቸው በዘመናቸው ስለሰሩበት እንጂ በከንቱ አይደለም ።

"ታላቁ የኑሮ ግብ ዕውቀት ማፍራት አይደለም ሠርቶ ማሳየት እንጂ" ብሎ ፈላስፋው ሀክስሌይ እንደተናገረው ሁሉም ወደ ሥራ ዓለም ሲሰማራ በእውቀቱ መጠን በዘመኑ ሊሠራ ነው ። ቢሆንም የሚያውቀውን ያለ ግብዝነት ፤ ያለ ማን አለብኝ በእውነት ሰርቶ ለወገኑ ለሀገሩ ለቤተ ክርስቲያኑ በሥራ ካልረዳ እርሱ ከማያውቁት በታች እንጂ አዋቂ ነው ማለት አይቻልም ።

"የኪስ መራቆት የወንጀል ምንጭ ሊሆን ይችላል" ሲል ፈላስፋው በርናርድ ሾው እንደተናገረው ሁሉ ሰው በዘመኑ ካልሠራ ገንዘብ ሊያገኝ አይችልም ። ካልሠራ ለእለት የሚጐርሳት እንጀራ እንኳን አያገኝም ። ስለዚህም በዘመናቸው ሠርተው እንዳይበሉ ሰርቀው መብላትን የሚመርጡ ብዙዎች ናቸው ። ሥራ ጠልተው እየዞሩ ምግብ ከመለመንና የሰው ፤ የሃገርና የቤተክርስቲያን ሸክም ከሚሆኑ በተለይ በሃገራችን በአሁኑ ጊዜ ሥራ ለሌላቸው ብዙ የሥራ መስክ ስለተከፈተ በዛ አነሰ ሳይሉ በዘመናቸው ሠርተው ቢበሉ መልካም ነው ። መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል ። "ከእናንተ ዘንድ በአንዱ ስንኳ እንዳን ከብድበት ሌሊትና ቀን በድካምና በጥረት እየሠራን እንኖር ነበር እንጂ ከማንም እንጀራን እንዲያው አልበላንም" 2ኛ ተሰሎ.ም.፫. ቍ.፰-፱ ።

አዎን እጅ እግር አእምሮና ጥበብ ያለው በፈጣሪው አምሳያ የተፈጠረው ሰው ሥራን ጠልቶ ሌላው የሠራውን ቢመለከት እዳ እንጅ ሥራ አይደለም ። ምክንያቱም ታላቁ መጽሐፍ ያልሠራ አይብላ ይላልና ። ከአሮጌ ዘመን ችግር ተላቆ በአዲሱ ዘመን ከደስታ ለመድረስ ሥራና ትእግሥት ያስፈልጋል ። ብዙዎች ይህ ትንሽ ሥራ ነው ምን ያደርግልኛል ያኛውም አድካሚ ነው ብለው ሥራ በማማረጥ ዘመናቸውን የሚጨርሱ ጥቂቶች አይደሉም ። ግን ተሳስተዋል እንጅ ሥራ ምንም እንኳን ቢያንስ በመልካም አስተሳሰብ በሥራ ወዳጅነትና በእውነተኛነት በዘመኑ ከተሠራ መጨረሻው ያማረ ይሆናል ።

አለበለዚያ ግን በሥራ ፈትነት ዘመን በተለወጠ ቁጥር በአምልኮ ጣዖት

ተከታዩን በ፻ኛው ገጽ ይመልከቱ



www.ethiopianorthodox.org

# ፓትርያርኩ የኃዘን መግለጫ መልእክት ላኩ



ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ጳውሎስ ፮ኛ እኔህ ነበሩ

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ፓትርያርክ ብፁዕወ ቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት የሮም ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን ፓፓ ጳውሎስ ስድስተኛ ከዚህ ዓለም በድንገት በሞት በመለ የታቸው የሐዘን መግለጫ መልእክት ልከዋል።

የሐዘን መግለጫውም መልእክት ሙሉ ቃል ከዚህ እንደሚከተለው ነው ።

ለሮም ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ
ቫቲካን ፤

በታላቁ መሪ ቅዱስ ፓፓ ጳውሎስ ስድስተኛ በድንገት ከዚህ ዓለም በሞት ማለፍ የተሰማማንን ጥልቅ ኃዘን ለቅዱስ ሲኖዶስና ለመላው የሮም ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን ምዕመናን እንገልጻለን . የሁላችንም ፈጣሪ የሆነው እግዚአብሔር በማያልፈው ዓለም በመንግሥተ ሰማያት ሰማያዊ ክብሩን ሰጥቶ ከቅዱሳን ነቢያትና ጻድቃን ጋር ነፍሳቸውን እንዲያኖርልን በአንድነት ወደፈጣሪያችን በጸሎት እንለምናለን ።

አባ ተክለ ሃይማኖት የኢትዮጵያ
ቤተ ክርስቲያን
ፓትርያርክ

## ሊቀ መንበሩ መልእክት ላኩ

(ከኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት)

ጓድ ሌተና ኰሎኔል መንግሥቱ ኃይለ ማርያም የጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግና የሚኒስትሮች ምክር ቤት ሊቀመንበር ፤ የብፁዕ ወቅዱስ ጳውሎስ ስድስተኛ የሮማ ካቶሊካዊት ቤተክርስቲያን ሊቀጳጳስን ዕረ

ተከታዩ ወደ ገጽ ፲፯ ዞሯል

# ከ35 ዐመታት በኋላ መጽሐፍ ቅዱስ በስሎቫክ ቋንቋ ታትሞ ወጣ

በተባበሩት የመጽሐፍ ቅዱስ ማኅበራት የሚዘጋጀው "የዓለም ሪፖርት" (ዎርልድ ሪፖርት) የተባለው መጽሔት በሐምሌ ወር 1978 ዓ.ም (እ.ኤ.አ)በአወጣው ቁጥር 100እትሙ መጽሐፍ ቅዱስ በዘመናዊ ስሎቫክ ቋንቋ በቼኮዝሎቫኪያ እንደ ታተመ አብስሮአል ። የትርጉሙ ሥራ 35 ዓመታት ወስዶአል ። ነገር ግን አሁን 16.000 ቅጂዎች በጥራዝ ክፍል ይገኛሉ ።መጻሕፍቱም በሐምሌ ወር 1978 ዓ.ም ለሕዝብ ይታደላሉ ። ለዚሁ እትም የሚሆነው ወረቀት በተባበሩት የመጽሐፍ ቅዱስ ማኅበራት ልግስና ቀርቦአል ። ነገር ግን 16.000 የመ.ቅ.ቅጂዎች በቂ አይደሉም ፤ ስለዚህም የቼኮዝሎቫኪያ በዓለ ሥልጣኖች 50.000 የመ.ቅ. ቅጂዎች እንዲጨምሩ ከስሎቫክ ወንጌላዊት የሉተራን ቤ ክርስቲያን ጋር ተስማምተዋል ።

ዜናው የተበሠረ ፦ በቅርብ ጊዜ በብራቲላቫ ከፕሮፌሰር ዶክቶር ጃን ሚችልኮ የሉተራን ቤተ ክርስቲያን ሊቀ ጳጳስ ጋር ተወያይተው በተመለሱት በተባበሩት የመ.ቅ.ማ. ለአ.ሮፕ ጸሐፊ በሆኑት በአሌቫን ሉይን ነው ። ይህ ሥራ በተባበሩት የመ.ቅ.ማ. እንደሚካሄድ ፤ ቅዱሳት መጻሕፍቱም ፦ ለማከፋፈል መካከለኛ ወይሚሆን ወደ ሉተራን ቤተክርስቲያን ማተሚያ ቤት በሚቀጥለዉ ዓመት እንደሚላኩ ይጠበቃል ።የተባበሩት የመጽሐፍ ቅዱስ ማኅበራት እንደ ሌሎች ሀገሮች በምሥራቅ አውሮፓ መጽሐፍ ቅዱስን ለማደል የሚመለከቱ የመንግሥት ሕጎችን በጥብቅ እንደሚከተሉ ጳጳስ ሚችልኮና የቼኮዝላቫኪያ የባህል ሚኒስቴር ዋና ሥራ መሪ ርማጡን በጥብቅ ተነጋግረዋል ።

ሁለተኛው የስሎቫክ መ.ቅዱስ ሕትመት በመዘጋጀት ላይ ሳለ በተራ ቀንቋ ቼኮዝሎቫኪያዊ መጽሐፍ ቅዱስ ለማሳተም በፕላኑ መሠረት ሥራው ቀጥሎአል።1979 ዓ.ም (እ.ኤ.አ.) የትውፊታዊው ክራሊስ መጽሐፍ ቅዱስ አራተኛ ክብረ በዓል ይሆናል ፤ እንዲሁም በአዲሱ የቼኮዝ መጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም ይታወሳል ።

ይኸው አዲሱ የቼኮዝ መ.ቅ. በቼኮዝሎቫኪያ ይታተማል ወረቀቱም በተባበሩት የመ.ቅ.ማ. ይገባል በ1968 እና በ1973 መካከል የቼኮዝሎቫኪያ የመ.ቅ.ድርጅት 120.000 የቅዱሳት መጻሕፍት ቅጂዎችን አስገብቶአል በቼኮዝሎቫኪያ አብዛኛው ቤተ ክርስቲያን የሮማ ካቶሊክ ነው ። ሌሎች አብያተ ክርስቲያናትም ይገኛሉ። ለምሳሌ ፦ የቼኮዝላቫኪያ ወንድማማች ቤተ ክርስቲያን፡ የሰባት ቀን አክባሪዎች፡ መጥምቃውያን ሜተድስቶችና ቼኮዝላቫኪያዊት የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ይገኛሉ ።


## ዐዋጃዊ ፈቃድ ለስላቫኒያን ወንጌሎች

የዩጎዝላቭ በዓለ ሥልጣኖች በአዲስ ስላቮኒያን ትርጉም አራቱ ወንጌሎች በሉብልጃን እንዲታተሙ ፈቀዱ ። የትርጉሙም ጓድ ሥራውን በመቀጠል ላይ ነው አዲስ ኪዳንንም በሙሉ በሁለት ዓመታት ውስጥ ለማጠናቀቅ ተስፋ ያደርጋል ። በ1978 ፍጻሜ ላይ ወይም በ1979 መጀመሪያ ላይ አራቱ ወንጌሎች በተራ ቋንቋ በስሎቬንያን ለሕትመት ይዘጋጃሉ ሙሉ አዲስ ኪዳንም በ1980 ዓ.ም. ይታተማል ሲል የዓለም ዜና (ዎርልድ ሪፖርት) ቁጥር 100 ሐምሌ 1978 የወጣው እትም ገልጦአል ።



www.ethiopianorthodox.org

# ዘመናዊ የንብ ርባታ ዕቅድ በአንደራቻ መድኃኔ ዓለም ቤተ ክርስቲያን



ለዘመናዊው የንብ ርባታ ዘመናዊ ቀፎ

የአንዳራቻ መድኃኔ ዓለም ቤተ ክርስቲያን በከፋ ክፍለ ሀገር በከፋ አውራጃ ከቦንጋ ከተማ በግምት 10 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ይገኛል ።

ቤተ ክርስቲያኑ በጣም ጥንታዊና ብዙ ሊቃውንትም የነበሩበት ትልቅ ገዳም እንደነበር ይነገራል የሕንፃው አሠራርና በውስጡ የሚገኙት ከቡሉኮ የተሠሩ የቅብ ሥዕሎች ለቤተ ክርስቲያኑ ጥንታዊነት ምስክሮች ናቸው ።

ይሁንና ከጊዜ ወደ ጊዜ እየመነመነ በመሄድ ላይ ያለውን የገዳምነቱን ሕይወት መልሶ ለማቋቋምና በአካባቢውም አዲስ የቤተ ክርስቲያን ትምህርተ ልደት ለመመሥረት ይቻል ዘንድ አንድ የመተዳደሪያ ዕቅድ በማስፈለጉና ከዚህም የተነሣ የአካባቢ ጥናት ተደርጐ በተገኘው ውጤት መሠረት ዘመናዊ የንብ ርባታ ቢዘጋጅ የተሻለ መሆኑ ታምኖበታል ።

ጥናቱን በማካሄድ ረገድ በአውራጃው የሚገኙ የንብ ርባታ ኃላፊዎችና አስተዳደሩ እንደዚሁም ጉዳዩ የሚመለከታቸው ሁሉ ተባባሪዎች ከመሆናቸውም በላይ የአካባቢውም የገበሬ ማኅበር አንድ መቶ ያህል ዘመናዊ የንብ ቀፎዎች ሊያስቀምጥ የሚችል ቦታ መንጥሮ በማዘጋጀት የሚረዳ መሆኑ ታውቋል ። ሥራውንም የሚያስተባብሩና የሚከታተሉ የልማት ኮሚቴ አባሎች ተመርጠዋል ።

ለንብ ርባታው የተመረጠው አካባቢ በዓመት ሦስት ጊዜ ለማር የሚሆኑ አበባዎች እንደሚያብቡ የተረጋገጠ ሲሆን በማር ምርት በኩል ጥሩ ውጤት ሊገኝ እንደሚችልና ዕቅዱም ተስፋ የሚጣልበት እንደሆነ ይታመናል ።

ይህንኑ ሥራ በቅርብ የሚከታተሉ ባለሙያዎችም በቅድሚያ መዘጋጀታቸው አስፈላጊ በመሆኑ ከአካባቢው የዚሁ የንብ ርባታ ልምድ ያላቸው ሁለት ሰዎች ተመርጠው በክፍለ ሀገሩ ንብ ርባታ ጣቢያ እንዲሠለጥኑ ታስቧል ።

የንብ ርባታውን ዕቅድ ሥራ ለመጀመርና ሥራውን ለሁለት ዓመታት ያህል ለማካሄድ በጠቅላላው $47.258.08 እንደሚያስፈልግ በጥናት የቀረበው ሪፖርት ያመለክታል ።

ይሁንና የኮሚሽኑ ጽ/ቤት ከዓለም አብያተ ክርስቲያናት ማኅበር በተለይ ለአነስተኛ እቅዶች "ሚኒ ፕሮጀክት" ማቋቋሚያ ከተመደበው ገንዘብ ለዚህ እቅድ $20.000 (ሃያ ሺህ ብር) ርዳታ ያገኘ መሆኑ ታውቋል ። ዕቅዱንም በሥራ ላይ ለማዋል ይቻል ዘንድ በቅድሚያ ሊዘጋጁ ለሚገባቸው ቁሳቁሶችና ለመሳሰሉት መግዣ ይውል ዘንድ እስካሁን $5.500 (አምስት ሺህ አምስት መቶ ብር)በብፁዕ አቡነ ዮሴፍ የሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ አማካኝነት ከፍያ ተደርጓል ።

የልማትና ክርስቲያናዊ ተራድኦ ኮሚሽን በገንዘብ ብቻ ሳይሆን የረዳው የፕሮጀክቱን ጠቅላላ ጥናት በማከናወንና ዕቅዱንም በሚገባ በማዘጋጀት ጭምር ነው ።

ይህን ዕቅድ በማስብና ከሥራ ላይ እንዲውል በይበልጥ ከደከሙት መካከል ብፁዕ አቡነ ዮሴፍ፣ መምሬ አባተ ኃይሉና ሌሎችም የቤተ ክርስቲያን ልጆች ይገኙበታል ።

የንብ ርባታው መቋቋም ከላይ ከተጠቀሱትና ለቤተ ክርስቲያኑ መተዳደሪያ ሊፈጥር ከመቻሉም በላይ ፤

1. ለአካባቢው ችግረኛ ቤተሰብ ልጆች የትምህርት ዕድል እንዲያገኙ ለማድረግ ፤
2. ለመሃይምናን ማንበብና መጻፍ ለማስተማርና የቤተ ክርስቲያንንና ዘመናዊውን ትምህርት ለማስፋፋት ፤
3. ወደፊት ለማቋቋም ለታሰበው የካህናት ማሠልጠኛ ት/ቤት ሥራ ማስኬጃ ገቢ ለማስገኘት እንደሚረዳ ይታመንበታል ።

በዚሁ አካባቢ የካህናት ማሠልጠኛ ት/ቤት ለማቋቋም እቅድ መኖሩንና ይህም ሥራ "መና ለዓለም" ከተባለው ርዳታ ሰጭ ድርጅት በሚገኘው ገንዘብ እንደሚከናወን ፤ የት/ቤቱንም የአምስት ዓመት በጀት ድርጅቱ እንደሚሰጥ ፤ የድርጅቱ ባለሥልጣን የሆኑት ፕሮፌሰር ሃያር እንደራቻ ተገኝተው ቦታውን ዙረው በጐበኙበት ወቅት ቃል የገቡ መሆኑን ብፁዕ አቡነ ዮሴፍ ገልጸዋል ።

የዚህ እቅድ ሥራ ተከናውና ሥራው በሚጀመርበት ጊዜ የአካባቢው ምዕመናን በብዙ ረገድ እንደሚጠቀሙ ተስፋ ይደረጋል ። እቅዱ ተሟልቶ የሥራ ፍሬ በሚታይበት ጊዜ ስለዚሁ ሰፋ ያለ ዜና ለማቅረብ እንሞክራለን ።

## ትዳር እንደ ቀልድ ...

ከ፯ኛው ገጽ የዞረ

ደሳች ኑሮ በአሳዛኝ ሁኔታ ይለወጣል ። ይኸም በጊዜ እጥረት ከምናደርገው ምርጫ በኋላ የሚሆን ውጤት ነው ለትክክለኛ የኑሮ አመሠራረት ግን ሰፋ ባለ ጊዜ በተጨማሪ የሁለቱም ተፈቃቃጅነት ዋናውን ቦታ መያዝ አለበት

ተከታዩ ወደ ገጽ ፲፬ ዞሯል

# የመስቀሉ ነገር

መስቀል ስሙ እንደሚያመለክተው የተመሳቀለ ማለት ነው ፤ ይህም ማለት አንድ ቀና ያለ ዕንጨት በትክክል ከቆመ በኃላ እንደ ገና ሌላውን ዕንጨት በተተከለውላይ ሲያጋድሙበት መስቀል ይሆናል ።

ለምሳሌ ተ ፊደል ራሱ የመስቀል ቅርጽ የያዘ ነው ሁለተኛም ሰው በትክክል ከቆመ በኃላ ሁለት እጆቹን የቀኙን ወደ ቀኝ የግራውንም ወደ ግራ ቢዘረጋው የመስቀል ቅርጽ የያዘ ምልክት ይሆናል የመስቀል ቅርጽ እንደዚህ ሲሆን መስቀል በጥንታውያን ሰዎች ይልቁንም በአይሁድ ዘንድ እጅግ የተናቀና የርግማን የውርደት ምልክት ሁኖ ይታይ ነበር ። ወንጀል ሠርቶ የተገኘው ሁሉ በመስቀል ላይ ተሰቅሎ ይሞት እንደነበር ታላቁ የሃይማኖት መጽሐፍ አብራርቶ ይገልጸል ።

እንዲያውም መስቀል በጣም የተናቀ እንደነበር በግልጥ የሚታየው የካህናት አለቆችና ምእመናኑ ሁሉ ትንሹም ትልቁም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ያዋረድን መስሏቸው በዕለተ ዓርብ በጲላጦስ ፊት ቀርቦ በሚመረመርበት ጊዜ አንድ ሁነው ያሰሙት የነበረው ቃል ስቀለው ስቀለው እሱን ካልሰቀልክ የቄሳር ወዳጅ አይደለህም የሚል ነው ይህ ራሱ መስቀል ምን ያህል በሕዝቡ ዘንድ የተናቀ እንደ ነበር ያመለክተናል ።

አዎ መስቀል በጥንታውያን ሰዎች ዘንድ በዚህ መልክ ይኑር እንጂ በእኛ በክርስቲያኖች ዘንድ ክርስቶስ ከተሰቀለበት ወዲህ ግን መስቀል ከፍ ያለ ክብር ያለውና የመንፈሳዊ ነጻነት የክርስትና አርማ ነው ።

ይኸውም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ ተሰቀለበትና ደሙ ስለ ፈሰሰበት አጋንንት የሚሸሹበት በሽተኞች የሚፈወሱበት ታላቅ ምልክትና የእግዚአብሔር ኃይል የሚገለጥበት ሁኖ ስለተገኘ ነው ከዚህም ሌላ የሰው ልጅ መንፈሳዊ ነጻነቱን አጥቶ ብዙ ዘመናትን ካሳለፈ በኋላ እንደ ገና ወደ ቀደመ ክብሩ ሊመለስ የቻለው ክርስቶስ በተሰቀለበት መስቀል ኃይል ነው ክርስቲያኖችም ሁሉ መስቀል ኃይላችን ነው መስቀል አምባችን ነው መስቀል መጠጊያችን ነው እያሉ የሚዘምሩት ከዚህ የተነሣ ነው ሐዋርያ ቅዱስ ጳውሎስም ከመስቀል ሌላ ለክርስቲያኖች መመኪያ እንደ ሌላቸው ሲያስገነዝብ ከጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መስቀል በስተቀር ሌላ ትምክህት ከእኔ ይራቅ ሲል ገልጦ ተናግሯል ።

መስቀል ለእኛ ለክርስቲያኖች ታላቅ ኃይልና ጥበብ ሲሆን ለሰነፎችና ምሥጢሩ ላልገባቸው አላዋቆች ግን ሞኝነት ነው ። ይህንንም ሲያብራራ ቅዱስ ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ሰዎች በጻፈው መልእክቱ በ1ኛ ቆሮ 1፡22 ላይ "መቸም አይሁድ ምልክትን ይለምናሉ ግሪካውያንም ጥበብን ይሻሉ ካለ በኋላ እኛ ግን የተሰቀለውን ክርስቶስን እንሰብካለን ይህንንም ስናደርግ በአይሁድ ዘንድ መሰናክል በአረማውያንም ሞኝነት ይመስላቸዋል ለተጠሩት ግን አይሁድም ቢሆኑ የግሪክ ሰዎችም ቢሆኑ መስቀል የእግዚአብሔር ኃይል ነው ሲል የመስቀልን ኃይል አጉልቶ ጽፏል ።

እኛ ክርስቲያኖች መስቀልን ስናከብረው በአንድ አንድ ሐሳበ ቢሶች አስተያየት የምናመልከው ይመስላቸዋል ። መስቀሉን ይሳለማሉ በማለት ይዘብቱብናል እኛ ግን መስቀሉን የምናከብረውና የምንሳለመው ክርስቶስ የሠራልንን መልካም ሥራና መከራውን ለማሰብ ነው ። ግን የመስቀል ክብር በብሉይና በሐዲስተጽፎ ስለምናገኘው የእነሱን አስተሳሰብ ከምንም አንቆጥረውም ብሉይ ኪዳን የመስቀልን ክብር ሲገልጥ "ወንሰግድ ውስተ መካን ኀበ ቆመ እግረ እግዚእነ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከቆመበትና እግሩ ከተቸነከረበት እንሰግዳለን ብሏል መዝ 130 ፣ 7

የክርስቶስ እግር የቆመበት መስቀል መሆኑን መገንዘብ አስፈላጊ ነው ሐዲስ ኪዳንም በከፍሉ መስቀልን ስለሚጠሉና ስለሚነቀፉ ሰዎች ሲያስገነዝብ የሚከተለውን ጽሑፍ አስፍሮ ይገኛል ። ብዙዎች ሰዎች ለክርስቶስ መስቀል ጠላቶቹ ሁነው ይመላለሱ እንደ ነበሩና አሁንም እንዳሉ ብዙ ጊዜ ስለ እነእርሱ አልኋችሁ አሁንም ሳይቀር እያለቀስኩ እላለሁ የእነዚያ ሰዎች ማለት መስቀልን የሚጠሉ መጨረሻቸው ጥፋት ነው ፤ ሆዳቸው አምላካቸው ነው፡ ክብራቸው በነውራቸው ነው ፤ ሐሳባቸውም ሰማያዊ ሳይሆን ምድራዊ ነው ካለ በኋላ መስቀል የሚወዱ ሰዎችና መስቀል የእግዚአብሔር ኃይል መሆኑንም የሚያምኑ ሰዎች ግን እኛ ቤታችን በሰማይ ነውና ከዚያም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን እንጠባበቃለን ሲል በሰማይ ያለውን ቤታችንን ያበሥራል ።


እኛም መስቀልን የምናከብረውና በአንገታችንም አሥረነው የምንታየው በሌላ ምክንያት ሳይሆን የእግዚአብሔር ኃይል ስለ ተገለጸበት መንፈሳዊ ነጻነት ስለ ተገኘበት ከዚያም ሌላ ከሲኦል ወደ ገነት ከመግዛት ወደ ነጻነት ከሞት ወደ ሕይወት የተሸጋገርንበት ታላቅ ድልድይ ሁኖ ስላገኘነው ነው ።

ምናልባት የመስቀልን ኃይል ያልተገነዘቡ አንዳንድ ሰዎች ቢኖሩ መስቀል የመከራ ምልክት መሆኑን ሊያውቁት ይገባል ። ነገር ግን ስንኳንስ የባሕርይ አምላክ እጅና እግር የተቸነከረበትና ክቡር ደሙ የፈሰሰበት ዕፀ መስቀል የጳውሎስ ልብስ እንኳ ድውይ ሲፈውስ ጋኔን ሲያወጣ እንደ ነበር በሐዋርያት ሥራ በም. 19፡12 ላይ ተጽፎ እናገኛለን ። በዚህ ምክንያት ነው እንጅ መስቀልን የምናከብረው በሌላ አለመሆኑን ማስተዋል ያስፈልጋል በሌላ በኩል ደግሞ የክርስቶስ ተከታዮች የሆን ሁሉ መስከረም 17 ቀን የመስቀልን በዓል በታላቅ ሥነ ሥርዓት የምናከብርበት ዋና ምክንያት የታላቁ ቆስጠንጢኖስ እናት እሌኒ ከቁስጥንጥንያ ተነሥታ ወደ ኢየሩሳሌም ተጉዛ በብዙ ድካም የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስን መስቀል አስቆፍ

ተከታዩ ወደ ገጽ ፲፩ ዞሯል



# ከቤተ ልሔም እስከ ደብረ ቁስቋም ።




ከእጅጉ ረታ

"እነሆ የጌታ መልአክ በሕልም ለዮሴፍ ታዶቶ ሄሮድስ ሕፃኑን ሊገድለው ይፈልገዋልና ተነሣ ሕፃኑንና እናቱን ይዘህ ወደ ግብፅ ሽሽ ፤ እስክነግርህም ድረስ በዚያ ተቀመጥ አለው ። እርሱም ተነሥቶ ሕፃኑና እናቱን በሌሊት ያዘና ከጌታ ዘንድ በነቢይ ልጄን ከግብፅ ጠራሁት የተባለው እንዲፈፀም ወደ ግብፅ ሄደ ። ሄሮድስም እስኪሞት ድረስ በዚያ ኖረ" ማቴ፡2፡ 13 - 15

ዮሴፍም ሕፃኑንና እናቱን ይዞ ወደ ምድረ ግብፅ ስለመሰደዳቸው ወንጌላዊው ባጭሩ ጠቅሶ ከማለፋ በስተቀር ወንጌሉን ለመጻፍ የተነሳበት ዋና ምክንያት ይህ ባለመሆኑ ዝርዝር ታሪኩ ውስጥ አልገባም ። ስለ ጌታ ልደትና ስለ ሕፃንነቱ ዜና ከዚህኛው ወንጌላዊ ይልቅ ስፋ አድርጎ የጻፈልን ቅዱስ ሉቃስም ይህን ወደ ምድረ ግብጽ የተደረገ ሽሽት ጨርሶ አላነሳውም ። ይሁን እንጂ እመቤታችን መለኮታዊ ልጅዋን ይዛ ፤ ከዮሴፍና ከሰሎሜ ጋር ተጉዛ በፈርዖኖች ምድር ያሳለፈችው የሦስት አመት ተኩል የስደት ዜና ከፍ ብሎ እንዳቀረብኩት በአራት በአምስት መስመሮች ብቻ ያከትማል ብሎ የሚያስብ የዋህ አንባቢ ይኖራል ብዬ አልጠራጠርም ።

እንዲህ እንደ አሁኑ ዘመን መንገዱ ባልሰለጠነበት ፤ የየብስና የአየር መገናኛ በላመቸበት ፤ የእንግዶች ማረፊያ ተዘጋጅቶ እንደ ልብ በማይገኝበት፤ ካሰቡበት ሥፍራ ዕለቱን ተነሥቶ ዕለቱን ገብቶ እፎይ ተብሎ ከማይታረፍበትያውም ሄሮድስን ከሚያህል መሠሪ ንጉሥ ፊት አዩኝ አላዩኝ ተብሎ በሽሽት የተደረገ ረጅምና አድካሚ ጉዞ ራሱን የቻለ አስደናቂ ሥራዎች የተፈፀሙበት የታሪክ ቅርስ ያለው መሆኑ አያከራክርም ።

ይህም ታሪክ ከመጀመሪያው ምዕት-ዓመት አንስቶ በምስራቁም በምዕራቡም የክርስትና ዓለም በቃልም በጽሑፍም ሲወርድ ሲዋረድ እስከ ዘመናችን ሊደርስ ችሏል ። ይልቁንም ሕፃኑንና እመቤታችንን ለማስተናገድ ዕድል የገጠማት ምድረ ግብፅ ስደተኞቹ በረገጡት ምድር ባለፉበት መንደር የተፈፀሙትን ድርጊቶች የሚያስታውሱትን የታሪክ ቦታዎች በታላቅ ቁም ነገር ጠብቃና ተንከባክባ ይዛ ትገኛለች ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንም እመቤታችን ጌታን ይዛ ወደ ምድረ ግብፅ ስለመሰደዷ ይብዛም ይነስም የሚያወሱ የታሪክ መጻሕፍት እንዳሏት የታወቀ ነው ። ይልቁንም ይህን የስደቷን መታሰቢያ በየትኛውም ሀገር ተደርጐ በማይታወቅ ልዩ ሥርዓት በየዓመቱ ከመስከረም 26 እስከ ሕዳር 6 ቀን ድረስ በ42 ቱ (ሦስት ዓመት ተኩል) የስደት ወራት አንፃር 42 ዕለታት መደብ ለዘመናት ስታከብረው ኖራለች ትኖራለችም ። ይህም ወራት የሰማዩ ደመና ገፎ ፤ የክረምቱ ወራት አልፎ ፤ ፀሐይ ጮራዋን የምትፈነጥቅበት፤ምድሪቱ በልምላሜ የምታጌጥበት ፤ በአበቦች (ጽጌያት) የምታሸበርቅበት ፤ ጊዜ በመሆኑ ወርሐ-ጽጌ ተብሏል ። ከ600 ዓመት በፊት የነበረው ኢሳይያስ ፤ "በትር ትወጽእ እምሥርወ እሴይ ወየዐርግ ጽጌ እምኑንዱ..." ብሎ ለእመቤታችን ትንቢት ተናግሮላት ስለነበር (ኢሳ 11 ፣1 ) ጥሩ አጋጣሚ መልካም አባባል ነው ለማለት ይቻላል ። በዚህም በወርሐ-ጽጌው ውስጥ ለዚህ ብቻ ሲባል ተዘጋጅቶ በየሳምንቱ እሁድ ሌሊቱን ሙሉ በቤተ ክርስቲያን የሚፈፀመውን ልብ የሚነካ መንፈስ የሚሰብር እስደሳች ስብሐተ ማኅሌት እዚህ ላይ መዘርዘሩ ቦታው ባይሆንም እመቤታችን ከምትወደው ልጅዋ ጋር የተቀበለችውን መከራ በማስታወስ በፈቃዳቸው በጾም በፀሎት ተወስነው ወርሐ ጽጌውን የሚያሳልፉ አባቶችናእና



www.ethiopianorthodox.org

# የጸሎት አስፈላጊነት

ከተስፋ ጥሩነህ

"ሁሉም የራሳቸውን ይፈልጋሉና የ ክርስቶስ ኢየሱስን አይደለም" ይህንን ቃል የተናገረው ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ሲሆን የሳከላቸው ለፊልጵስዩስ ሰዎች ነው ።

ሰብአዊ ጥበባትን ለማግኘት የተፈጥሮ ስጦታን ፣ ከፍ ያለ ብልሃትንና ብዙም ገንዘብን ይጠይቃል የጸሎት ኃይልና ጥበብ ግን እንደዚህ ያለ አይደለም፡ የጸሎት ኃይልና ጥበብ ብዙ ሀብት የሚጠይቅ አይደለም ። አነስተኛ እውቀት ያለው መሃይምን ሃብት የሌለው ድሃ ፡ ትንሹም ፡ ትልቁም ፡ ቅዱስ በሆነው የጸሎት ጥበብ ሊጠቀምበት ይችላል ። ጸሎት ከሰዎች የሚፈልገው ዋና ዋና ነገሮች አሉት ፣ እነርሱም ልምድና አለመሰልቸት ናቸው ።

ማንኛውም ሰው ያለማዘውተር ያለ ልምድ እውነተኛ የጸሎት ሰው ሊሆን አይችልም ። መሰልቸት ካለ ደግሞ አንድ ነገር ልምድ ሊሆን አለመቻሉ የታወቀ ነው ።

እነዚህ ነገሮች በጸሎት እየበሰልን ለመሄድ ከሚረዱን ዓይነተኛና የማይታለፍ ከሆኑት መካከል ጥቂቶቹ ናቸው መቼም ሁላችንም ጥዋት ተነስተን ወደሥራችን መሮጥ ፡ ቀንም ከሥራችን ጋር መታገል እንጂ ከምንሠራው ጋር ያሰብነውን ሁሉ እኛ ሠርተን የምናቃናው እኛም ተናግረን የምንፈጽመው እየመሰለን በድካማችን ብቻ እንመካለን እዚህ ላይ ነው ስህተታችን ፡ ሰው ደካማ ፍጡር በመሆኑ ከሚሠራው ሥራ ጋር የእግዚአብሔር ረድኤት ካልተጨመረበት ፈጽሞ አይሳካም ። ቤትን እግዚአብሔር ካልሠራ የሚሠሩ ሁሉ በከንቱ ይደክማሉ ተብሎ ተጽፎአልና፡

የእግዚአብሔር ቅዱስ ቃል አትለምኑምና ለእናንተ አይሆንም ። በምኞታችሁም ትከፍሉ ዘንድ በክፉ ትለምናላችሁና አትቀበሉም ይላል ።

በእርግጥም እግዚአብሔር ምህረቱንና ስጦታውን እንዲልክላቸው የሚጸልዩ ብዙ ሰዎች እንዳሉ ሁሉ ፡ እንደዚሁም በሌሎች ላይ መዓቱንና ቁጣውን መቅሰፍቱን እንዲያወርድባቸው የሚጸልዩ ብዙዎች ናቸው ።

እንዲያውም በሰዎችና ሰዎች መካከል ሁከት ፤ ብጥብጥ ፤ እንዲፈጠር የሚለምኑም ጥቂቶች አይደሉም ።

በሰበብ ባስባቡ ሁከት ሲነሳ ለእነርሱ ምቹ ስለሚመስላቸውና ሌላውም ሰላም ሲያጣ እነርሱ ሰላማውያን ሆነው የሚጠቀሙ እየመሰላቸው ሁከት ብጥብጥ ፡ ረብሻ እንዲነሳ የሚጸልዩት ብዙዎች ናቸው ።

ዳሩ ግን የእግዚአብሔር ፈቃድ ሁሉም እንዲድን እንጂ እንዲጠፉ ስላይደለ እነዲህ ዓይነቶቹ ሰዎች በከንቱ ይፈጫሉ በከንቱም ይጸልያሉ ።

እንዲህ ዓይነቶቹ ሰዎች የለመኑት ከንቱ ልመና ሳይፈጸም ሲቀር ደግሞ ሃይማኖት እንደሌለ ይገምታሉ ። እግዚአብሔርም ጸሎትን የማይሰማ አምላክ ይመስላቸዋል ።

ከዚህም የተነሳ እግዚአብሔር የለም ወደ ማለት ደረጃ ይሸጋገራሉ ።

የእነዚህ ሰዎች ሙሉ ስህተት ከአለማመን ላይ ነው ። መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ ጸሎት ሲያስተምር ፈቃድህ ይሁንልን እንዳንተ ፈቃድ እንጂ እንደኛ ፈቃድ አይደለም እንድንል ነው ። ይህን አውቀን የእኛ ፈቃድ ሳይሆን የእግዚአብሔር ፈቃድ እንዲሆን ከጸለይን እኛ ከምንፈልገው በላይ እግዚአብሔር ፈቃዳችንን ሊፈጽምልን ይችላል ። በዚያም ጊዜ እግዚአብሔር ቸር እንደሆነ ቀምሳችሁ እወቁ ተብሎ እንደተጻፈው የእግዚአብሔርን ቸርነት ወደማወቅ እንደርሳለን የእግዚአብሔርንም መኖር እንመሰክራለን ።

መቼም እያንዳንዳችን ጭንቀት ፣ አለብን እንደሰትም ። እንበሳጫለን ይህንን ሁሉ ችግራችንን በኃይላችን በችሎታችን ለማስወገድ እንጥራለን።ግን ኃይላችን ደካማ ስለሆነ ይህንን ሁሉ የእግዚአብሔር ኃይል ካልተጨመረበት በራሳችን ኃይል ብቻ ልናስወግደው ከቶ አንችልም ።

እንዲህ ዓይነት ችግር ሲገጥመን እግዚአብሔር በቅዱስ ቃሉ በጸሎት በምልጃ ከምስጋና ጋር በእግዚአብሔር ዘንድ ልመናችሁን አስታውቁ እንጂ በአንዳች አትጨነቁ ይላል ።

ስለዚህ እግዚአብሔር ለእኛ ከእኛ በላይ የሚያስብልን ስለሆነ ከሃይማኖት ፈቀቅ በማለት በከባድ ጭንቀት አየር ለመቧጠጥ መታገልና ዘወትርም ሕይወትን የብስጭት የጭንቀት አምባ ከማድረግ በእግዚአብሔር አምኖ እግዚአብሔርን መለመን አስፈላጊ ነገር ነው ።

ምናልባት እንዴት እንደምንጸልይ አናውቅ ይሆናል። ነገር ግን ራሳችን ለጸሎት ከተዘጋጀን መንፈስ ቅዱስ ስለምን ጸልየው ያስተምረናል ፣ የእግዚአብሔር ቅዱስ ቃል ስለዚህ ነገር እንዲህ ይላል ።

እንዴት እንደምንጸልይ እንደሚገባን አናውቅም ። ነገር ግን መንፈስ ራሱ በማይነገር መቃተት ይማልድልናል ።

ሮሜ 8 ፡ 26 ። መቼም ማንም ሰው ጸሎት በሚያደርግ ጊዜ ለጸሎት የተዘጋጁትን መጻሕፍት በማገላበጥ መድገሙን ያስታውስ እንደሁ እንጂ ጸሎቱ በምን ዓይነት ሁኔታ እንደሚደርስና እንደሚፈጸም ሊያውቅ ከቶ አይችልም ።

ስለዚህ እኛ ማለት ያለብን ፈቃድህ ይሁንልን ማለት እንጂ እግዚአብሔር ስለሚፈጽምልን ጉዳይ ስለአልሆነ ዘወትር ፈቃድህ ይሁንልን እንበል ።



# የርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ጳውሎስ ፮ኛ ዜና ዕረፍት

ከፍቅርና ሰላም ጋዜጣ የተገኘ

በቅዱስ ጴጥሮስ ወንበር ፪፻፷፩ኛ ተከታይ የሆኑት ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ጳውሎስ ፮ኛ በተወለዱ በ፹፩ ዓመት ዕድሜአቸው በ፲፭ኛው ዘመነ ሥልጣናቸው ሐምሌ ፴ ቀን ፲፱፻፸ ዓ·ም· እንደግሪጎሪዊ ሰዓት አቆጣጠር ከሌሊቱ በ፫ ሰዓት ከአርባ ደቂቃ ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተዋል ። የሞቱትም የበጋ ወራት ማረፊያዎች በሆነው በሮማ ከተማ አቅራቢያ በሚገኘው ከስቴልጋን ደልፎ በተባለው ቤተ ርእስ ሊቃነ ጳጳስት ነው ። ቀደም ሲል እቀኑ ላይ የልብ ድካም ተሰምቷቸው ሕመሙ እየጠናባቸው ሂዶ ነበረ ዜና አሰራጪዎች ገልጸው ነበር ።

ስለቅድስናቸው አሟሟትና የሕይወት ታሪክ ወደፊት ሰፋ አድርገን እስክናቀርብ ፤ መንፈሳዊ አባትነታቸውን ያጡ ካቶሊካውን በሙሉ ባታላቅ ኃዘን ተውጠው በሚገኙ በትባሁኑ ጊዜ በተለይ በአፍሪካዊነታችን ጭምር ዘወትር ከትዝታቸው ጋር እየተጣመሩ ሳይታወሱን ሊያልፉ የማይችሉትን ከብዙው በጥቂቱ አንዳንድ ነገሮች ልንጥቀስ እንወዳለን ።

ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ጳውሎስ ፮ኛ ፤ ለመላው የሰው ዘር ይልቁንም ልማትንና ተገቢ ኑሮን ከእፎይታ ለሚጠብቁ ሕዝቦች ሰላም እጅግ አድርጎእንደሚያስፈልጋቸው በመረዳትና የክርስቶስን መንግሥት በማተኮር ለሰላም የታገሉ ፤ ስለ ደካሞችና ስለሰው ልጅ መብቶች የተሟገቱ ፤ በርእሰ ሊቀ ጵጵስና ዘመናቸው ሁሉ የኢየሱስ ክርስቶስ መልእክት በምላቱና በእውነተኛ



ኢ.አ በሚገኘው የካቶሊክ ካቴድራል ጸሎተ ፍትሐት በተደረገበት ወቅት

ዓ·ም ያፕፍሪካን ምድር የረገጠ የመጀመሪያው ርእስ ሊቃነ ጳጳሳት በመሆን ዑጋንዳን ጎብኝተዋል ። የኡጋንዳ ሰማዕታት በመባል የታወቁትም ፲ ካቶሊካውያን በብጹዓንነት ደረጃ ታውቀው እንዲከበሩ እንደ ኢ-አቆጣጠር በ፲፱፻፷፬ ዓ· ም· ያወጁ ር· ሊ· ጳጳሳት ጳውሎስ ፮ኛ ናቸው ።

በዘመናቸው የአፍሪካውያን ካርዲናሎች ብዛት ወደ ፲፪ ደርሱዋል ላገር ተወላጆች ማዘጋጃ የሚሆኑ ዘርዓ ክህነቶች እጅግ ከፍ ባለ ብዛት ተከፍተዋል ። የዚሁም ድካም ፍሬ ፤ በውጭ ልዑካን እግር እየተተኩ ቤተክርስቲያናቸውን የሚመሩ ተወላጆች ከዓመት ወደ ዓመት

መልኩ በሥራ ላይ እንዲውል ለሕዝቦች ለመሪዎቻቸውም ከመምከርና ከመውቀስ ያላቋረጡ ከመሆናቸው በላይ የአፍሪካ እድገትና ባለ እኩል መብት መሆን ከልብ የሚተጉበት ጉዳያቸው ነበር ።

እንደ ኢ- አቆጣጠር በ፲፱፻፷፱

## ሊቀ መንበሩ ...

ከ፳ኛው ገጽ የዞረ

ፍት ምክንያት በማድረግ ትናንት የኃዘን መግለጫ መልእክት አስተላልፈዋል ።

ጓድ ሊቀመንበር መንግሥቱ የኃዘን መግለጫውን መልእክት ያስተላለፉት በራሳቸውና በጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ ስም ነው ።



www.ethiopianorthodox.org

በሚያስደስት ፍጥነት እየበዙ መሄዳቸው ሲሆን ፤ በሌላ በኩል ደግሞ የካቶሊክ ቤተክርስትያን ተከታይ የሆኑ የአፍሪካ ልጆች ቁጥር በእጥፍ አድጎ ዛሬ ወደ ፵ ሚሊዮን ለመድረስ በቅቷል ።



አምባሳደሮች ሥርዓተ ጸሎቱን ሲካፈሉ

የቅድስናቸው እስከሬን ረቡዕ ነሐሴ ፫ ቀን ከካስቴል ጋንዶልፎ ወደሮማ ተወስዶ ቅዳሜ ነሐሴ ፮ ቀን ፲፱፻፸ ዓ-ም ሥርዓተ ቀብራቸው ተፈጽሟል ። በአዲስ አበባም በካቴድራል ልደታ ቤተክርስትያን በዚሁ ቀን ስለቅዱስነታቸው እረፍት ቅዳሴና ፍታት ተደርጓል ።

## ኢትዮጵያን ያስታወሱበት የመጨረሻ ንግግራቸው

ጳውሎስ ስድተኛ በመጨረሻው የሕይወታቸው ሰሞን ካሰሟቸው ኢትዮጵያን የሚመለከት ስለሆነ በተለይ በዚህ አጋጣሚ ሳንጠቅስ ልናልፈው አልቻልንም መልእክቶች አንደኛው በተለይ ሐምሌ ፲፮ ቀን ፲፱፻፸ ዓ-ም በካስቴል ጋንዶልፎ ሁነው ብዙ ሕዝብ በተሰበሰበበት ባሰሙት ንግግር እንዲህ ብለው ነበር ።

«እነሆ እኛ በዚህ በሚያምርና ምቹ በሆነ ጸጥታም በሰፈነበት ስፍራ ነን ። እዚህም በመገኘታችን ለእግዚአብሔርና ለቤተክርስትያን አገልግሎት የምናውለው አዲስ ጥንካሬ እንሸምትበታለን ብለን ተስፋ እያደረግን ለፈጣሪ ችርነት ወሮታችንን እናሰማለን ። ይሁን እንጂ በብዙ ችግሮች ተተብትቦ ከሚገኘው በዙሪያችን ካለው ዓለም የተገለልን አይደለንም ። በተለይም በዛሬው ቀን ለኛ እጅግ ውድ ወደሆነችው ኢትዮጵያ ልቦናችን ያተኩራል ። ያች አገር ብዙ ተስፋ ያላት ለጥንታውያን የ አ ሪ ት ትውፊቶችና ለከበሩ የክርስትያን ባህሎች ውርስ ባለቤት የሆነች አገር ናት ። ብዙ ብሔረ ሰቦች ፤ ብዙ ዓይነት ፍላጎቶች ፤ ብዙ ፕሮብሌሞች ያሉባትም ናት ።

በሰብአዊ ርኅራኄ ምክንያት ስሞኑን በተሰሙት ጥሪዎች አማካይነት የዚያች አገር አንዳንድ ክፍሎች ምን ያህል ከባድ ፈተና እንደወደቀባቸው ለማወቅ ተችሏል ። የካቶሊክ ቤተክርስትያን ድርጅቶችና ሌሎችም ተቋሞች በወንድማማችነት ትብብር ተዋሕደውና ባገሪቱ ባለሥልጣኖች ፈቃጅነት ተደግፈው ለነዚያ ችግሩ በይበልጥ ለጠናባቸው ክፍሎች እርዳታ ማቅረብ ከጀመሩ ብዙ ጊዜያቸው ነው ። የኢትዮጵያም ቤተክርስትያን የወገኖቿን ችግር ለማቃለል ከፍ ባለ መስዋዕትነት ራሷን ያሰለፈች መሆኗን ሰምተናል ። ጉዳዩ ግን አልፎ አልፎ እንደሚያጋጥምና መፍትሔው እዚያ በዚያው እንደሚገኝለት ቀላል ነገር የሚገመት አይደለም ። መስዋዕቶቹ ለቁጥር የሚያታክቱ ዕድልም ሁና በተለይ ይበልጥ ደካሞችና መከላከያ የሌላቸው ፤ አብዛኛውንም ጊዜ ለመቅሰፍቱ መነሻ ፈጽሞ ባዕድ የሆኑ ሰዎች የሚሳቀዩበት ስፉ የሆነ ችግር ነው ። »

## ከቤተ ልሔም …

ከ፲፩ኛው ገጽ የዞ.

በስተደቡብ ሲል በምትገኝ አንዲት የውሃ ጉድጓድ ስላገኙ ጌታ ፡ እመቤታችን ፡ ዮሴፍና ሰሎሚ ስድስት ወራት ያህል ያስ ብዓቸው በዚያ አሳልፈዋል ። በዚችም በተቀደሰች ቦታ ከዘመናት ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ ድንቅ ድንቅ ሥራዎችና ልዩ ልዩ ተአምራት ስለሚደረግባት ከግብፅ አውራጃዎች ሁሉና ከሌሎችም ሥፍራዎች በአውቶቡስ ፡ በግመልና በከብት ኰቴ የእመቤታችንን የቃል ኪዳን በረከት ለመቀበል የሚጐርፈው ሕዝብ ስፍር ቁጥር የሌለው መሆኑ ተረጋግጧል ። ይችውም ቦታ ደብረቁስቋም ናት ። በነገራችን ላይ እንጦጦ ከመጨረሻው የአውቶቡስ ማቆሚያ አጠገብ ያለችውን የቁስቋም ቤተ ክርስቲያን በየወሩ የመድኃኔዓለም ዕለት (27) ሄደው ተሳልመው ያውቃሉን? ሄደው አያውቁ እንደሆን እስቲ አንድ ጊዜ ብቅ ይበሉና የሚፈፀመውን ተአምር በዓይንዎ ለማየት ይሞክሩ ። የልዑል እግዚአብሔርን ቸርነት ፡ የእመቤታችን አማላጅነት ያለጥርጥር ይረዱበታል ።

## ዘመን ካልሠሩበት አሮጌ ነው

ከ፮ኛው ገጽ የዞ.

ጥ እንዳይሻር መሬት ቆፍረው በመቅበር ይህንንና ያህንን በመሰለ በአሮጌ ልማድ አዲሱን ዘመን በመጥፎ ሥራቸው አሮጌ ዘመን ለሚያደርጉት የሚቆያቸው ዋጋ ሀዘት ይሆናል ።

እንግዲህ እያንዳንዳችን አዲሱን ዘመን ያለምንም ሥራ በዋዛ በፈዛዛ ለውጠ ነው ከሆነ ድሪቶ እንጂ አዲስ ዘመን አይባልም ። ምክንያቱም አንድ ሰው ኮቱ ተቀዶበት በተቀደደው ወገን አዲስ ኮት ለበሰ ለማለት አንችልም ። ስለዚህ እኛም ያለፈውን ዘመን በደንብ ሠርተን አሳልፈነው ካልሆነ ይህም አዲስ ዘመን ለኛ አሮጌ ዘመን እንጂ አዲስ ዘመን አንለውም ። ምክንያቱም ዘመን ካልሰሩበት አሮጌ ነውና ።

ብርሃን ተድላ



✕ የመጽሐፍ ቅዱስ ዓምድ ✕

# የመስቀሉ ቃል

## የእግዚአብሔር ኃይል ነው

፩ ፡ ቆሮ. ፩ ፡ ፲፰ ።

### የተሰቀለውን ክርስቶስ ስለመስበክ

እኔም ወንድሞቼ ሆይ ወደ እናንተ በመጣሁ ጊዜ በቃልና በጥበብ ብልጫ ለእግዚአብሔር ምስክርነቱን ለእናንተ እየነገርሁ አልመጣሁም ። በመካከላችሁ ሳለሁ ከኢየሱስ ክርስቶስ በስተቀር እርሱም ስለተሰቀለ ሌላ ነገር እንዳላውቅ ቆርጬ ነበርና ። እኔም በድካምና በፍርሃት በብዙ መንቀጥቀጥም በእናንተ ዘንድ ነበርሁ ፤ እምነታችሁም በእግዚአብሔር ኃይል እንጂ በሰው ጥበብ እንዳይሆን ፤ ቃልም ስብከቴም መንፈስና ኃይልን በመግለጥ ነበረ እንጂ ፤ በሚያባብል በጥበብ ቃል አልነበረም ።

በበሰሉት መካከል ግን ጥበብን እንናገራለን ፤ ነገር ግን የዚችን ዓለም ጥበብ አይደለም የሚሻሩትንም የዚችን ዓለም ገዦች ጥበብ አይደለም ፤ ነገር ግን እግዚአብሔር አስቀድሞ ከዘመናት በፊት ለክብራችን የወሰነውን፤ ተሰውሮም የነበረውን የእግዚአብሔርን ጥበብ በምሥጢር እንናገራለን ። ከዚችም ዓለም ገዦች አንዱ እንኳ ይህን ጥበብ አላወቀም ፤ አውቀውስ ቢሆን የክብርን ጌታ ባልሰቀሉም ነበር ፤ ነገር ግን ፡—ዓይን ያላየችው ጆሮም ያልሰማው በሰውም ልብ ያልታሰበው እግዚአብሔር ለሚወዱት ያዘጋጀው ተብሎ እንደ ተጻፈ ፤ እንዲህ እንናገራለን ። መንፈስም የእግዚአብሔርን ጥልቅ ነገር እንኳ ሳይቀር ሁሉንም ይመረምራልና ለእኛ እግዚአብሔር በመንፈሱ በኩል ገለጠው ። በእርሱ ውስጥ ካለው ከሰው መንፈስ በቀር ለሰው ያለውን የሚያውቅ ሰው ማነው? እንዲሁም ደግሞ ከእግዚአብሔር መንፈስ በቀር ለእግዚአብሔር ያለውን ማንም አያውቅም ። እኛ ግን ከእግዚአብሔር እንዲያው የተሰጠንን እናውቅ ዘንድ ከእግዚአብሔር የሆነውን መንፈስ እንጂ የዓለምን መንፈስ አልተቀበልንም ። መንፈሳውያን ነገር ከመንፈሳዊው ነገር ጋር አስተያይተን መንፈስ በሚያስተምረን ቃል ይህን ደግሞ እንናገራለን እንጂ የሰው ጥበብ በሚያስተምረን ቃል አይደለም ። ለፍጥረታዊ ሰው የእግዚአብሔር መንፈስ ነገር ሞኝነት ነውና አይቀበለውም ፤ በመንፈስም የሚመረምር ስለሆነ ሊያውቀው አይችልም ። መንፈሳዊ ሰው ግን ሁሉን ይመረምራል ራሱ ግን በማንም አይመረመርም ። እንዲያስተምረው የጌታን ልብ ማን አውቆት ነው ? እኛ ግን የክርስቶስ ልብ አለን ። ፩ኛ. ቆሮ. ፪ ፩ — ፲፮ ።

እነኝህ ንባቦች የተቀዱት ከመጽሐፍ ቅዱስ ነው ይህን ካነበቡ በኋላ አንድ መጽሐፍ ቅዱስ ገዝተው እንዲያነቡ እናሳስባለን ።


## የኢትዮጵያ የመጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር

የፖ. ሣ. ቁ. 30750
ስልክ 122033
አዲስ አበባ

የፖ. ሣ. ቁ. 700
ስልክ 113455
አሥመራ



www.ethiopianorthodox.org



# ምእመናን ሆይ !

በክርስቶስ የተመሠረተች ቤተ ክርስቲያን ሀብቶቿ ምእመናን ናቸው የቅድስት ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን እያፈሰሰ·ጉዳት አስከትሏል፤የሥላሴ ፍቅር የጠራችሁ፤ ለቤተ እግዚአብሔር መጠገኛ እጃችሁን እንድትዘረጉ ተጋብዛችኋል ።

የአድባሉ ኮሚቴ



# ኢ.ኦ.ተ.ሐ.ድ

ማሳሰቢያ ለምእመናን በሙሉ

የኢትዮጵያን ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነትና ታሪክ ፣ ጸዋትወ ዜማዎችንና ቅዳሴዎችን ፣ መንፈሳዊ ዘመናዊ መዝሙሮችን ፣ ትምህርቶችንና የል ማት እንቅስቃሴዎችን ሁሉ እየተከታተለ በቴፕ እየቀረጸ ለቤተ ክርስቲያኒቱ ቋሚ ቅ ርስ ያስቀምጣል ። ይህንኑ ለሚፈልጉ ግለ ሰቦችም ሆኑ ድርጅቶች የካሴት ክር ላቀ ረቡ ያገልግሎት ሁለት ብር ብቻ በማስከፈል ይሰጣል ።

ለዚሁ ጥያቄ ቢኖርዎ ከድርጅቱ በመምጣት ወይም ስልክ በመደወል ለመ ረዳት ይቻላል ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ሐዋርያዊ ድርጅት
የካሴት ሐዋርያ አገልግሎት

ስልክ ቍ. 116616
የመል. ሣ. ቍ. 3137
አዲስ አበባ



www.ethiopianorthodox.org